ግንቦት 6ቀን 2015ዓ.ም.(May 14, 2023 )



**<u>ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ከዚህ ዓለም የተለዩበትን 24ኛ ዓመት አሥመልክቶ የወጣ መግለጫ!</u>**

ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደዩስ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት(የመዐሕድ)ፕሬዝዳንት! የዛሬ 24ዓመትግንቦት 6ቀን 1991ዓም(እ.አ.አ ሜይ14ቀን 1999ዓም) በፔንሲልቫንያ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ፊላደልፊያ አሜሪካ አገር በህክምና ላይ ቆይተው ከዚህ ዓለም እንደተለዩ ይታወቃል። ሕዝባችን ይህንን ዕለት አሥቦት የሚውለው በታላቅ ሀዘንና ቁጭት ነው፡፡

ፕሮፌሰር! በ1983ዓም የትህነግና የኦነግ ዕድምተኞች አማራን በማግለል ያካሄዱትን ፀረ አማራ ኮንፈረንስ፣የኢትዮጵያን ሀገራዊና ሕዝባዊ አንድነት የመናድ ተግባር፣የኮንፈረንሱን ምንነት፣ የመጣውም የጎሳ ፖለቲካ ችግር ሊያሥከትል እንደሚችል ከመናገር አንሥቶ ፣በአማራው ላይ የመጣውን የመከራ እሳትም ለማጥፋት በቀዳሚነት የተሰለፉ እና ድምፃቸውን አጉልተው ያሠሙ ብቸኛው የቁርጥ ቀን ልጅ ነበሩ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋካልቲ ዲን የነበሩት ፕሮፌሠር አሥራት! የዩኒቨርሲቲ ምሁራን በመረጧቸው መሠረት በሰኔ 1983ቱ ኮንፈረንስ ላይ በመገኘት፣በተለይ የኤርትራን መገንጠል፣በአጠቃላይ "መገንጠል"እና ሌሎችም የኢትዮጵያ መተዳደሪያ እንዳይሆኑ የተቃወሙ <u>ብቸኛ</u> የጉባዔ ተሳታፊ ነበሩ። ከዚህ ኮንፈረንስ በኋላም የዩኒቨርሲቲ ምሁራንን በመወከል በተቋቋመው የሽግግር መንግስት በተወካዮች ምክር ቤት አባልነት እንዲሳተፉ ተደጋጋሚ ጥሪ ተደርጎላቸው አልተቀበሉትም።

ፕሮፌሰር! ዐማራው ዐማራ ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ፣ከሌሎቹ በተለዩ የግፍ ፅዋ ቀማሽ እና ተቆርቋሪ የሌለው መሆኑን በመገንዘባቸው፣ከጨርሶ መጥፋት ለማዳን፣በዘርና በጎሳ እየለዩ እርስ በርስ የማጫረስ አፍራሽ ፖሊሲን የዘረጋውን ሥርዓት ለመታገል ቆርጠው ከተነሱ ወገኖቻቸው ጋር በመምከር የመደራጀትን አስፈላጊነት አምነውበት መዐሕድን አቋቋሙ፡፡ በፕሬዚዳንትነትም መሩት።

በአነግና በኦህዴድ ኦሮሞዎች! ዐማራው በሐረር፣በአርባጉጉ፣በበደኖ፣በአረካ፣በአሰቦት ገዳም፣በአሩሲና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል መታሰሩ፣መሰደዱ፣ህይወቱ እያለ ዓይኑ ሲጎለጎል፣ቆዳው ሲገፈፍ፣ቤት ዘግተው ሲያቃጥሉት፣ወደገደል ሲወረውሩት፣ሥጋውን ቆርጠው "ብላው እያሉ" ሲያሰቃዩት፣ ሕፃናት ከእነቤተሰቦቻቸው ሲታረዱ፣የዕርጉዞች ሆድ ተቀዶ ሽሉ ሲጣል፣ የዐማራው ልጃገረዶች ሲደፈሩ፣ ሲዋረዱና ተማርከው በባርነት ሲያገለግሉ፣አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉና ሌሎችም ተዘርዝረው የማያልቁ የዘር ማጥፋት ሰቆቃዎች ሲፈፀሙበት፣ፕሮፌሰር አሥራት! ዙሪያ ገባውን በጠላት ቢከበቡም፣ ችግርና ፈተና ሳይበግራቸው፣ከፊት ለፊታቸው የተጋረጠውን ግዙፍ ኃይልና አደጋ ከምንም ሳይቆጥሩ፣ በቁርጠኝነት በመቆም በዚህ በቀውጢ ሰዓት ከማንም ቀድመው ይህንን እኩይ ሥርዐት ያለመታከት በማጋለጥ የአማራው ሕዝብ የሚፈፀምበትን ወንጀል እንዲረዳና እንዲታገል፣ዓለምም እንዲያውቀው በማድረግ፣በታላቅ ቆራጥነት ታግለው "ዴሞክራሲያዊ ነኝ "ባዩን ትነግን እርቃኑን ማስቀረታቸው አርአያነቱ ምንጊዜም የማይረሳ ነው።

ይህ የመዐሕድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊ ተቀባይነት ማግኘት ፣ትህነግን ዕርፍት ነሥቶት የተለመዱ ሥድቦችን በመደርደር፣ ወደእሥርና ግድያ ቢሄድም፣ትግሉን ሊያሥቆመው እንደማይችል ተረዳ፡፡ ሥለዚህ ትህነግ! <u>አማራው አንድ ሆኖ ለመብቱ</u> እንዳይቆም፣ በአማራ መካከል እየገባ የሚበትን <u>**አደገኛ መርዝ**</u> መትከልን መረጠ፡፡

ይህም <u>**አደገኛ መርዝ!**</u> ከትግሬ ጎሳ ጀምሮ የተለያዩ ጎሳዎችን ያቀፈውን "<u>ኢሕዴን</u>" የሚባለውን አማራ ጠል ድርጅት በአንድ ቀን ጀምበር የአማራ ሥም ሠጥቶ ወደ "<u>ብአዴን</u>" በመቀዬር፣በአንድ በኩል አማራውን እንደጨቋኝ ሥሎ "ብሔራዊ ጭቆና አለ" ብሎ በክልሉ ህገ መንግሥት ውስጥ አሥፍሮ፣በሌላ በኩል ለአማራ የቆመ ድርጅት በማሥመሠል፣ከፋፍሎ እንዲያዳክም እና ከእነፕሮፌሰር አሥራት ጭምር ጠንካሮቹን እየመረጠ በመግደልና በማሥገደል ሥራ እንዲሠማራ ማድረግ ነው፡፡ዛሬም <u>አማራን እየከፋፈሉ ለመጨረስ እንዲያመቸው፣በኢትዮጵያ ሥም የሚጠራው</u> <u>የአቢይ ኦሮሞ መከላከያ፣ፌደራልና ደህንነት (የ16ኛው ክፍለ ዘመን የጋላ ወረራ ዓይነት)ወረራ በአማራ ሕዝብ ላይ ሲያካሂድ፣</u> <u>ቀደም ሲል አማራ ላለማለት ነፍጠኛ እያሉ ሲጨርሱት እንደኖሩት፣ዛሬ ደግሞ ፋኖ እያሉ ሲጨርሱት፣</u> መንገድ ከፋቹና ጠቋሚው፣ ገዳይ አሥገዳዩ ይኸው <u>የብአዴን/አዴፓ/ብልፅግና</u> ነው፡፡ የዚህ ድርጅት!የመከፋፈልና የመግደል ማሥገደል ተልዕኮ ትህነግ(ኢሕአዴግ) በኦሮሞ(ብልፅግና)ሲተካ፣ የሚቆምሳይሆን፣<u>"ከሥርዓቱ፣ከህገመንግሥቱናከዘርፌደራሊዝሙ"</u>ጭምር፣ነቅተን፣ተደራጅተን እሥካላሥወገድነው ድረስ የአማራው ሠቆቃ ይቀጥላል።እሥካሁን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው።

Comment [AF1]:

ፀረ አማራዎቹ ትግሬዎች በብአዴን ተባባሪነት! ፕሮፌሰር አሥራትን በማምጠጫ ዕድሜያቸው ወቅት የሀሰት ክሶችን ፈጥረው፣ከእሥርቤትና ከፍርድ ቤት ምልልስ ባሻገር ለበርካታ በሽታዎች ተዳርገው ህክምናም እንዳያገኙ ተከልክለው፤አምስት ዓመት አንገላተውና አሠቃይተው በቁመና ከገደሏቸውና እንደማይድኑ ካረጋገጡ በኋላ፣ለይስሙላ ህክምና ሆሥፒታል ገቡ፣ቀጥሎም ወደውጭ አገር ሄዱ፡፡ ቢሄዱም ተስፋ በማይሰጥ ሕክምና ቆይተው አረፉ። ይህ ድርጊት የሚያሳዬው ዘረኞቹ በአማራው ሕዝብ ላይ ያላቸውን መረን የለቀቀ ጥላቻ ነው፡፡አማራው በወቅቱ ይህ ገብቶት ነቅቶና ተደራጅቶ ቢሆን ኖሮ የቅርቡ የትግሬ፣የዛሬው የኦሮሞ ወረራ አይፈፀምብንም ነበር፡፡

ዘረኞችንና ባንዳዎችን በልበሙሉነትና በጀግንነት ሲታገሉ፣በማይቀረው የሠው ልጅ መጨረሻ በሆነው ሞት በአካል ከእኛ የተለዩን ፕሮፌሰር አሥራት!ጉልበታቸውን፣ዕውቀታቸውን፣ገንዘባቸውንና ዕምነታቸውን፣ብሎም ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡት፣በቅድሚያ የአማራን ሕዝብ ህልውና ተግባራዊ ለማድረግ፣ቀጥሎም ለአገርና ለሕዝብ አንድነትና ነፃነት ሲሉ ነበር።ይህ ለእኩልነትና ለዲሞክራሲያዊ ሕይወት ግኝት የከፈሉት አቻ የለሽ መሥዋዕትነት፣በታሪክ ዓምድ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ከመያዙም ባሻገር፣ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የሚኖር ነው። አሥራት!የሕዝባችን፣የሠንደቃላማችን፣የታሪካችን፣ የአንድነታችን፣የክብራችን፣የአይበገሬነትና የአባቶቻችን ዕውነተኛ ቅርስ ከመሆናቸው ጋር ተዳምሮ ቀሪ ሥራዎቻቸውን ለመወጣት ከፀና ዓላማና ከጠራ ዕይታ ጋር በማገናዘብ ህልውናችንን ለማሥጠበቅ ተገቢውን መሥዋዕትነት መክፈል ይጠበቅብናል፡፡መሥዋዕትነቱ ቀጥሎ ክቡር ህይወት የተቀጠፈበት ተልዕኮ ግቡን ሊመታ የሚችለው ህልውናችንንና መብታችንን እሥካሥከበርን ድረስ ነው፡ይህንን ተግባራዊ ሳናደርግ ከቀረን ሕዝባችንና መጭው ትውልድ ቅር እንጅ ይቅር አይለንም፡፡የተሠዉ ወገኖቻችንም አፅም፣ አጥንት ሆኖ መዋጋቱም አይቀሬ ከመሆኑም በላይ፣ከታሪክ ተወቃሽነትም መዳን አይቻልም፡

ዛሬ ፕሮፌሰር አሥራት ቢያልፉም፣ዓርማውን አንግበው፣በአይበገሬነት ሞትን እየሞቱ ለመታገል የቆረጡ እንደ እንጉዳይ የፈሉና እሳት የላሱ ሚሊዮን ወጣት አሥራቶች መፈጠራቸው እሠዬው የሚያሠኝ ነው፡፡

ከፕሮፌሰር ትምህርት ሠጭ ንግግሮች አንዷን ለላሙና ሠንዝሬ ፅሁፌን ልግታ፡፡

> **"ዛሬ ታላቁ የዐማራው ጠላት ዐማራው ነው።አንዳንድ የደላውና ዐወቅሁ ባዩ፣የዐማራ ድርጅት በመቋቋሙ አልሥማማም እያለ ሲዋልል፣ሌላው ደግሞ በጠቋሚነት፣በአሳባቂነት፣በአድርባይነት፣በገዳይነት የገዛ ወንድሙን ለዕለት ሆዱ ፍላጎት ሲል ከፍተኛ በደል እያደረሰ ነው።እሥካሁን ድረስ የተሠራው ተሠርቷል።ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንደነኚህ ያሉትን፣ጠላትነታቸውን እንዲያውቁ ማድረግና ይሉኝታም ስፍራ የሌለው መሆኑን በጥብቅ ልናሳስብ እንወዳለን።በሌላ በኩል ሌላው የዐማራ ክፍል ተኮላሽቶ፣ተኝቶ በማንቀላፋት ላይ ይገኛል።ይህ ክፍል ቢቃጠልም እንኳ ሲሠማው ስላልቻለና አልነቃም ብሎ ስለቀረ፣ያለው ዕድል እንደሚባለው"ዐማራው ሲተኛ የሚበላው ጅብ ነው።"" ነበር ያሉት ።**

ይህ ችግር ዛሬም ተንሠራፍቶ ይገኛል።ፕሮፌሰር ያሉትን ሰምተን ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጠን ተነሥተን ቢሆን ኖሮ ይህ ዛሬ ያለው ችግር በተቀረፈ ነበር።ዛሬም ቢዘገይም አልመሸም፣ዕንወቅበት።

ይህን ካልኩ በኋላ የአሥራትን ውለታ እንዴት እንከፍላለን ሥንል፣ የትግል ዓርማቸውንና የመንፈስ ጥንካሬቸውን ተላብሰን በመታገል ነው።በኢትዮጵያ ምድር የዓሥራት ዓላማ ተግባራዊ እሥከሚሆን ድረስ ትውልድ ሁሉ ትግሉን መቀጠሉ ውለታ ከፋይነቱን የሚያረጋግጥ ይሆናል።

በመጨረሻ! ለአማራው ህልውናና አንድነት ቀናኢ የሆነው ሁሉ፣ፕሮፌሰር አሥራት!ታሪክና ትውልድ የማይረሳው ተግባር ፈፅመው በማይቀረው የሠው ልጅ መጨረሻ በሆነው ሞት፣ከዚህ ዓለም የተለዩበትን 24ኛ ዓመት አሥመልክቶ በታላቅ ሀዘን፣ ቁጭትና ወኔ አሥቦት እንዲውል እያስታወስን፣ይህን ዕለት ከሕዝባችን ተስፋና ድል ጋር አያይዞ የሚከበርበት ወቅት አሁን ባለው የጊዜና የሁኔታ ውስብስብነት ቢዘገይም አይቀሬ መሆኑን ሳናሰምርበት አናልፍም።

የፕሮፌሰር አሥራት ሥራ ህያው ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል!

ለአማራው ህልውና የሚደረገው ትግል እሥከድል ይቀጥላል!

ሞት ለፀረ-አማራዎች

አያሌው ፈንቴ